## ፍ ር ድ

1.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም በጥቅሉ አመልካች የተጠሪውን ዕዳ ያወራርድ በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሕብረት ስምምነትና የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ተጠሪው ለአመልካች መክፈል የሚገባውን የአገለግሎት ካሣ ክፍያና የሰባ ቀን የዓመት እረፍት ክፍያ በአግባቡ ለይቶ እንዲወስንና ከዚህ ውስጥ አመልካች ለተጠሪው መክፈል የሚገባውን ብር 13,211.69 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ አስራ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 መሠረት በማቻቻል ቀሪ ገንዘብ የሚኖር ከሆነ ለአመልካች እንዲከፈል እንዲያደርግ፤ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

ይህ ፍርድ ሚያዚያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



የሰበር መ/ቁ. 29866

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ
መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- ቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ወርቅነህ ምህረቴ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል የሚመሰረትበትን ሁኔታ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ተቀጥሬ ደመወዝ እየተከፈለኝ በጥቅምት 2 ቀን 1996 ዓ.ም በተሰጠኝ የውክልና ሥልጣን ድርጅቱን በጥብቅና ሥራ በማገልገል ላይ ሳለሁ አመልካች የስራ ውሌን ያቋረጠው ስለሆነ በአመልካች ሊከፈለኝ ይገባል ያሉትን ክፍያ በመዘርዘር በአማራ ክልል ደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ድርጅቱ ተጠሪን በሠራተኛነት አልቀጠረም፣ ደመወዝም አልከፈለም፤ የድርጅቱ ጠበቃ የነበሩት አቶ የስጋት ንጉሴ ሥራቸውን ሲለቁ አዲስ አበባ የሚገኙትንና የድርጅቱ የህግ አማካሪ የነበሩትን አቶ ጥበቡ ጋሹ የተባሉትን ግለሰብ መጥተው ደ/ማርቆስ አካባቢ ያለውን የድርጅቱን ጉዳይ እንዲከታተሉ ስንጠይቃቸው አዲስ አበባ ያለው ጉዳይ ብዙ ስለሆነ መምጣት አልችልም - ነገር ግን እኔ ደመወዝ እየከፈልኩት የእኔን ቦታ ሸፍኖ የሚሰራ ሰው ስላገኘሁ ድርጅቱ ውክልና ብቻ ይስጠውና የጥብቅና አገልግሎት ይስጥ በማለት በጠየቁን መሰረት ለአሁን ተጠሪ የውክልና ስልጣን ሰጥተናቸው ሲያገለግሉ ከመቆየታቸው በስተቀር ከእኛ ጋር የሥራ ውል የላቸውም፣ በመሆኑም

በመካከላችን የቅጥር ውል ሳይኖር ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በተጠሪ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚያስረዳው ተጠሪ በአመልካች መወከላቸውን ነው በተጠሪ የተቆጠሩት ምስክሮች የመሰከሩትም ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው መስራታቸውን እንደማያውቁ ነው፣ በአመልካች በኩል የተቆጠሩት ምስክሮች ደግሞ አመልካች የሰጠውን መልስ በሚደግፍ መልኩ መስክረዋል፣ በግራ ቀኙ የጋራ ምስክር ሆነው የተቆጠሩት አቶ ጥበቡ ጋሹ ቀርበው እኔ በስሬ ሌሎች ባለሙየዎችን እየቀጠርኩ በተመሳሳይ ሁኔታ በሌሎች ክልሎችም የሙያ ስራ ስለምሰራ ተጠሪንም በዚሁ መልክ ቀጥሬአቸው ደመወዝ እየከፈልኳቸው አመልካች በሚሰጣቸው የውክልና ሥልጣን በጥብቅና እንዲያገለግሉ ተደርጎ እኔ ከአመልካች ድርጅት ጋር ያለኝ ውል ሲቋረጥ ተጠሪ ሥራቸውን አቁመው በእጃቸው የሚገኙትን መዝገቦች እንዲያስረክቡ በነገርኳቸው መሰረት አስረክበዋል በማለት የመሰከሩ ስለሆነ አመልካች ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ስላላስረዱ በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ውል የለም፣ መካከላቸው የሥራ ውል ከሌለ ደግሞ ተጠሪ የሥራ ውልን መሰረት አድርገው ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መብት ስለሌላቸው ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2) መሠረት ውድቅ ተደርጓል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት የሥራ ውል በጽሁፍም ሆነ ያለጽሁፍ ሊመሰረት ስለሚችል ተጠሪ ያቀረቡት የውክልና ሥልጣን ማስረጃ በግራ ቀኙ መካከል ውል መኖሩን የሚያስረዳ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ለህጉ የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት ተጠሪ የጠየቋቸው ክፍያዎች አይገባቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሚዛናዊነት የጎደለው ነው በሚል ተጠሪ የጠየቋቸው ክፍያዎች ይከፈሏቸው ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሥራ ውል አለ የተባለው



በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ውል አለ ለማለት የቻለው በተጠሪ የቀረበው የውክልና ሥልጣን ማስረጃ በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የውል ግንኙነት እንደነበረ ያረጋግጣል በሚል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ በሁለት ወገኖች መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ውል በጽሁፍ ቢደረግም ባይደረግም ውጤቱ ተመሳሳይ መሆኑ የማያከራክር ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ግንኙነቱ በውል ላይ የተመሠረተ ሲሆንና ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ተቀጥረው ደመወዝ እየተከፈላቸው የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጡ መቆየታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት በአመልካች ተሰጥቷቸው የነበረውን የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ሲሆን ይህ ማስረጃ የሚያረጋግጠው አመልካች በተጠሪ ተወክለው እንደነበረ እንጂ ተቀጥረው ሲያገለግሉ እንደነበረ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል በግራ ቀኙ የጋራ ምስክር ሆነው የተቆጠሩት ግለሰብ ለአመልካች ድርጅት የጥብቅናና የህግ ማማከር አገልግሎት ሲሰጡ በነበረበት ወቅት ተጠሪን በመቅጠር ደመወዝ እየከፈሏቸው ከአመልካች በሚያገኙት የውክልና ሥልጣን ለድርጅቱ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ ያሰማሯቸው መሆኑንና ድርጅቱ ከእሳቸው ጋር የነበረው ግንኙነት ሲቋረጥም ተጠሪ ከድርጅቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነትም አብሮ የተቋረጠ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ከዚህ መረዳት ሚቻለው ተጠሪ የተቀጠሩት አመልካች ድርጅት በቀጠራቸው ግለሰብ እንጂ በአመልካች አለመሆኑ ራሳቸው ተጠሪ ባቀረቧቸው ምስክር የተመሰከረ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የውል ግንኙነት እንዳልነበረ ተገንዝበናል፡፡ በተጠሪና በአመልካች መካከል የውል ግንኙነት ካልነበረ ደግሞ ተጠሪ በአመልካች ላይ ከውል የመነጨ የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ አገልግሎቱን ሲሰጡ የነበረው ከአመልካች ጋር በነበራቸው የውል ግንኙነት መሆኑን ባላስረዱበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የውክልና ሥልጣን ማስረጃው በግራ